# ይለዩ፣ ያስወግዱ እንዲሁም ማጭበርበሮችን ሪፖርት ያድርጉ

## ማጭበርበርን ለመከላከል መመሪያ መጽሐፍ

### ለቅርብ ጊዜ ጥገኝነት ጠያቂዎች እና ስደተኞች

Amharic

የፌዴራል ንግድ ኮሚሽን (FTC) ሰዎችን ከማጭበርበሮች የሚጠብቅ የመንግስት ኤጀንሲ ነው።

የማጭበርበር አንዳንድ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች እዚህ አሉ። ከእነዚህ ምልክቶች ውስጥ አንዱን ካዩ፣ ያቁሙ። ይነጋገሩበት። ለFTC በ **ReportFraud.ftc.gov** ወይም 1-877-382-4357 ያሳውቁ።

በእንግሊዝኛ ማውራቱ ያስቸግሮታል? ሪፖርት ለማድረግ እንዲረዳዎት የሚያውቁት እና የሚያምኑትን ሰው ይጠይቁ።

# የማጭበርበር ማስጠንቀቂያ ምልክቶች

## አንድ ሰው ከከፈሉት ለእርስዎ ስራ ሊሰጡት ቃል ገብቶሎታል?

ለሥራ ቃል የሚገባሎት፣ ሥራ የሚያሰጦት ሰርተፍኬት፣ ወይም ሥራ በድብቅ የማግኘት ዕድል እሰጣለሁ ለሚል ሰው ፈጽሞ አይክፈሉ። እነዚያ ማጭበርበሮች ናቸው።

## አንድ ሰው የመንግስት ኤጀንሲ ነኝ ብሎ አስፈራራዎት ወይም ገንዘብ ጠየቀዎት?

መንግስት እርስዎን ለማስፈራራት ወይም ገንዘብ ለመጠየቅ አይጠራም።

## ግሪን ካርድ ለማግኘት ወይ የዲይቨርሲቲ ቪዛ ሎተሪ እንዲያሸንፉ አንድ ሰው ሊረዳዎት ይችላል ብሎት ነበር?

ለማመልከት ነፃ ነው አሸናፊዎቹም በዕጣ ነው የሚመረጡት። ማንም የማሸነፍ እድልዎን ሊጨምርሎት አይችልም።

## በስደተኛ ሁኔታዎ ላይ እርስዎን ለመርዳት ኖታርዮው ጥያቄ አቅርቦሎታል?

ስለ የስደተኛ ሁኔታዎ የህግ ምክር ከፈለጉ፣ ወደ  ጠበቃ ወይም እውቅና ያለው ተወካይ ይሂዱ። በጭራሽ ወደ ኖታርዮ አይሂዱ።

## የሆነ ነገር አሸንፈዋል የሚል ጥሪ፣ ኢሜይል፣ የጽሁፍ መልዕክት ወይም የማህበራዊ ሚዲያ መልእክት ደርሶታል? ክፍያ ግን አለው የሚል?

ለሽልማት አይክፈሉ። ያ ማጭበርበር ነው። ገንዘብዎን ያጣሉ።

## አንድ ሰው በስጦታ ካርድ፣ እንደ ዌስተርን ዩኒየን ወይም መኒ ግራም ባሉ ኩባንያዎች በኩል ገንዘብ ወይም ክሪፕቶፕ እንዲከፍሉ ጠይቆዎታል?

በዚህ መንገድ መክፈል አለብህ የሚሉት አጭበርባሪዎች ብቻ ናቸው። እንዳያደርጉት።

### የገንዘቡን የተወሰነ ክፍል እንድትመልስላቸው ከጠየቆት ሰው ቼክ አግኝተዋል?

ለቼክ በምላሹ ለሰው ገንዘብ አይስጡ። የውሸት ቼኮች  እውነተኛ ሊመስሉ እና ባንኩን ሊያታልሉ ይችላሉ። ገንዘቡን መልሰው መክፈል ይኖርብዎታል።

### የክሬዲት ካርድዎን፣ የባንክ ሂሳብዎን ወይም የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን የሚጠይቅ የጥሪ፣ ኢሜይል፣ የጽሁፍ ወይም የማህበራዊ ሚዲያ መልእክት ደርሶዎታል?

ያንን መረጃ በስልክ፣ በኢሜይል፣ በጽሁፍ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ ለሚጠይቅ ለማንኛውም ሰው በጭራሽ አይስጡ።

## እራስዎን እና መረጃዎን ይጠብቁ

- አስፈላጊ ወረቀቶችዎን ወይም መታወቂያ ካርዶችዎን ከእርስዎ ጋር አይያዙ።
- ምን እንደሆኑ እርግጠኛ ካልሆኑ በስተቀር በኢሜይሎች፣ በጽሁፍ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ መልእክቶች ውስጥ ያሉ ሊንኮች ወይም አገናኞችን አይጫኑ።
- የደዋይ መታወቂያ አይመኑ። አጭበርባሪዎች ማንኛውንም ስም ወይም ቁጥር በጥሪ መታወቂያዎ ላይ እንዲታይ ማድረግ ይችላሉ።
- ለሚደውል፣ ኢሜል ወይም ጽሑፍ ለሚልክ እና ከመንግስት ጋር ነን ለሚል ለማንም ሰው ገንዘብ አይላኩ።
- የመንግስት ማህተም ማለት ድህረ ገጽ ይፋዊ ነው ማለት አይደለም። በአድራሻው ውስጥ .govን ይፈልጉ።
- ከዩኤስ መንግስት ለስደት ቅጾች በፍፁም አይከፈሉ። ነፃ ናቸው።
- የሆነ ሰው ማንነትዎን የሰረቀ ከመሰሎት ለእርዳታ **IdentityTheft.gov** ይጎብኙ።

# ማጭበርበሮችን ወደ

## የፌደራል ንግድ ኮሚሽን (FTC) ሪፖርት ያድርጉ

## **ReportFraud.ftc.gov**

## ወይም 1-877-382-4357

### ማጭበርበሮችን ለምን ሪፖርት ማድረግ አስፈለገ?

ሪፖርትዎ የምታስቡላቸውን ሰዎች ለመጠበቅ ይረዳል። FTC አጭበርባሪዎችን እንዲዘጋ እና ሌሎች እንዳይታለሉ ያግዛል።

ማጭበርበርን ስለማስወገድ የበለጠ ይረዱ:

**consumer.gov**

የፌደራል ንግድ ኮሚሽን (FTC)
consumer.gov
ኦገስት 2022